# የተጀመረው ልማት በቀለም አቢዮት ናፋቂዎች አይገታም

ኢብሳ ነመራ 1/27/14

የእያንዳንዱ ሉዐላዊ አገር ውሳኔ፤ ሕግ፣ ፖሊሲ . . . የአገሩን ህዝብ ጥቅምና ፍላጎት ቀዳሚ ያደረገ ነው። አገራት ከሌሎች አገራት ጋር የሚመሰርቱት ግንኙነት፣ በዓለም አቀፍ ተቋማት ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎም የአገራቸውን ህዝብ ጥቅምና ዘላቂ ህልውና ማስጠበቅ ላይ የተመሰረተ ነው። ምንም አይነት የህዝብ ጥቅምና ፍላጎት፣ ለሌላ አገር ወይም ዓለም አቀፍ አካል ጥቅም ፍላጎት መስዋዕት መደረግ የለበትም። መጠቃቀም ላይ የተመሰረተ ግንኙነት የዓለም አቀፍ ግንኙነት መሰረታዊ መርህ ነው። የአንድ አገር የመንግስት ስርዓትና ዓለም አቀፍ ግንኙነት በዚህ መርህ የተመሰረተ ሊሆን ይገባዋል።

የሌላ አገር መንግስት ወይም ዓለም አቀፍ ተቋም፣ የራሱን ሕዝብና የሚወክለውን መንግስት ጥቅምና ፍላጎት ወደጎን አቆይቶ *የእኔን ሀገርና ህዝብ ጥቅም በቀዳሚነት ያስጠብቅልኛል* ብሎ መጠበቅ የዋህነት ነው። ሁሉም አገር የራሱን ጥቅም ነው የሚያስጠብቀው። መንግስታት፣ አለም አቀፍ ተቋማትም ቢሆኑ *ሰብአዊ መብት ማስከበርን ተቀዳሚ ግባቸው አድርገው በአገሬ ጉዳይ ጣልቃ ይገባሉ* ብሎ መጠበቅ ስህተትነቱ የሚያይል መሆኑን የሚያሳዩ ተሞክሮዎችም አሉ።

ታዲያ ሰሞኑን አንድ ከዚህ ጋር የተያያዘ ወሬ ሰምተናል። የአውሮፓ ህብረት ዲፕሎማት የተባሉ 12 ሰዎች የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲን (አንድነት) አመራሮችን አነጋገሩ የሚል ወሬ። የአውሮፓ ሕብርት ዲፕሎማቶች የተባሉ ሰዎች የአንድነት አመራሮች ማነጋገር ያን ያህል ዋጋ የሚሰጠው ጉዳይ ባይሆንም በጥንቃቄ መጤኑ ግን ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ለዚህም የዚህ ፅሁፍ የትኩረት ነጥብ አድርጌዋለሁ፡፡

ከአውሮፓ ህብረት መጡ የተባሉት 12 ዲፕሎማቶች አንድነት ፓርቲን ያነጋገሩት አጠቃላይ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ያለበትን ሁኔታ እንዲሁም የአውሮፓ ህብረት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የሚኖረውን ሚና የተመለከቱ አጀንዳዎች ዙሪያ መሆኑ መገናኛ ብዙሃን ነግረውናል፡፡ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ጉዳይና የአውሮፓ ሕብረት በአገሪቱ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጥ የሚኖረው ሚናም የአንድነት ፓርቲ ጉዳይ ሳይሆን የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የህዝብ ውክልና የሌለው አንድነት የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚመለከተው ጉዳይ ላይ ከውጭ አካል ጋር መነጋገሩ ጉዳዩን በጥንቃቄ ማጤንን አስፈላጊ ያደርገዋል ፡፡

አንድነት ፓርቲ ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማካሄድ የተመዘገበ ፓርቲ ነው። ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ(ኢዴፓ)፣ ከቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ፣ ከኢትዮጵያ ፍትህና ዴሞክራሲ ፓርቲ፣ . . . ሌሎችም በክልላዊ መንግስት ደረጃ ለመንቀሳቀስ ከተመዘገቡ በአጠቃላይ 80 ገደማ የሚሆኑ ፓርቲዎች ጋር ተመሳሳይ ሕጋዊ መብትና ነፃነት ያለው ፓርቲ ነው። በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ከሌላ መንግስትም ይሁን ዓለም አቀፍ ተቋም ጋር ተነጋግሮ መንግስታት ወይም ተቋማት በኢትዮጵያ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ እንዲገቡ የመጠየቅ፣ የመገፋፋት የህግም የሞራልም መብትና ስልጣን የለውም።

በመሆኑም ከአውሮፓ ህብረት መጡ ከተባሉ ሰዎች ጋር የአገሪቱ ፖለቲካዊ ሁኔታ ምን እንደሚመስልና ሕብረቱ በዚህ ውስጥ የሚኖረው ሚና ምን መሆን አለበት የሚለው ጉዳይ ውስጥ ገብቶ ማቡካቱ ተገቢ አይመስለኝም፡፡ ከጀርባው አንዳች ቀፋፊ ነገር መኖሩንም ይጠቁማል፡፡

በቅድሚያ አንድነት ተጨባጭ የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታ ላይ አንድ የውጭ አካል ሊያውቀው የሚገባውን ዕውነታ በገለልተኝነት መናገር የማይችል ከፓርቲው አቋም የመነጨ ውስን ዕይታ ያለው ፓርቲ ነው። አንድነት ፓርቲ በአገሪቱ መሰረታዊ የፖለቲካ ጥያቄና የህገመንግስቱ ምሰሶ የሆነው የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብትና የአገሪቱ ፌዴራላዊ አወቃቀር ላይ ያለው አቋም ከወደቁት ስርአቶች የሚመዘዝና አሮጌ ነው፡፡ በመሆኑም አሁን ያለውን የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ሁኔታ በዚህ አሮጌ መነፅር አንጋዶ የሚመለከት ፓርቲ ነው።

ለረጅም ግዜ ፓርቲውን በፕሬዝዳንትነት የመሩትና ከቀናት በፊት ፓርቲውንም የተሰናበቱት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ " ፓርቲው ለኢተዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰንና ራስ በራስ የማስተዳደር መብት የሰጠውን የሕገመንግስቱ አንቀፅ 39 ጠቅሰው፣ አንደነት ይህን አንቀፅ የማይቀበል መሆኑን "ፓርቲ ለሕዝብ መብት ደንታ የሌለው ነው" ሲሉ የገለፁትን ለዚህ አስረጂነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

የአንድነት ዕውነተኛ አቋም በንጉሰነገስቱና በወታደራዊ ደርግ የመንግስት ስርአት የነበረውን አሃዳዊ የመንግስት ስርአት መመለስ ነው። በተለይ በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሰረተውን ፌዴራላዊ አወቃቀር አንድነት አይቀበልም፣ ፓርቲው ይህን አቋሙን በይፋ ሲገልፅ ቆይቷል። ይሁን እንጂ አሃዳዊ የመንግስት ስርአት ምንም ተቀባይነት እንደሌለው ስለተረዳ በተለየ ሁኔታ ይህንኑ አወቃቀር ያመጣል በሚል ምልከታ "ፌዴራላዊ ሥርአትን እደግፋለሁ ግን አወቃቀሩ በብሄር፣ ብሄረሰብ ላይ ሳይሆን በመልከአ ምድር ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት" የሚል አቋም ነው ያለው።

አንድነት ይህን አቀም የመያዝ ሕገመንግስታዊ መብት ያለው መሆኑ ሳይዘነጋ፣ ይህ አቋሙ ኢትዮጵያ የምትባለዋን አገር የመሰረቱት፣ ለዘመናት በተካሄደና ከፍተኛ መስዋዕትነት በጠየቀ ትግል ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ፣ እርስ በርስ ተከባብረው በእኩልነት ለመኖር ቃል ኪዳን በገቡት፣ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ዘንድ ፍፁም ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ግን ተጨባጭ እውነት ነው። አንድነት ኢትዮጵያ ውስጥ ደጋፊዎች አሉት ከተባለ በተወሰኑ ትላልቅ የአገሪቱ ከተሞች የሚኖሩ ያረጀው ስርአት ቅሪቶች ብቻ ናቸው።

የአንድነት ደጋፊዎች በርካታ የሚመስሉት ማንኛውም ጩኸት፣ መልዕክቱ ምንም ይሁን ምን በቀላሉ በሚሰተጋባባቸው ትላልቅ የአገሪቱ ከተሞች በተለይ አዲስ አበባ ውስጥ ያሉ በመሆናቸው ነው፡፡ ፓርቲው የያዘው አመለካከት ያረጀና ያፈጀ በመሞት ላይ ያለ በመሆኑ እደሚሄውን ለማራዘም በነፃ ፕሬስ ሽፋን በተቋቋሙ ልሳኖቹ አማካኝነት እየተንፈራገጠ ሰቅጣጭ የጣዕረ ሞት ድምፅ ስለሚያሰማ ይህ ሰቀጣጭ እሪታ ጆሮ ስለሚጠልፍም ነው ደጋፊዎቹ ብዙ የሚመስለው። አንድነት ከዚህ ያለፈ በአዲሲቱና በመጪዋ ኢትዮጵያ ስፍራ ያለው ፓርቲ አይደለም። በመክሰም ላይ ያለ አመለካከትን የተመረኮዘ ጉደንጹ የተማሰ ፓርቲ ነው።

ብሄሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ፣ በቋንቋቸው እየሰሩና ልጆቻቸውን እያስተማሩ በመቻቻልና በመከባበር ላይ የተመሰረተ አንድነት ኖሯቸው የሚኖሩባት ኢትዮጵያ ለአንድነት ጠንካራ አንድነት ያላት ሳተሆን የተከፋፈለች፣ ልትበታተን የተቃረበች ሆና ነው የምትታየው። አንድ ብሄር ፣ ሁለትና ሶስት ቦታ ተሸንሽኖ በተለያየ አስተዳደር ስር ወድቆ፣ በሌላ በኩል ከአንድ በላይ ብሄሮች፣ ብሄረሰበችና ሕዝቦች በአንድ ላይ ተጨፍልቀው፣ አንዳንዶቹም መኖራቸውን የሚናገ ምልክት እንኳን እስኪጠፉ ተሸንሽነው በሌሎች ተውጠው በከፋፍለህ ግዛ ስልት አቅማቸው እንዲዳከም ተደርጎ ብሄራዊ መብትና ነፃነታቸውን ተነጥቀው ይኖሩባት የነበረውን አሃዳዊ ስርአት ናፋቂ ፓርቲ ነው፡፡

ይህ ብሄሮች ብሄረሰቦች፣ ማንነታቸው ዕውቅና ተነፍጎት ለብሄራዊ ጭቆና የተዳረጉበት፣ የህዝብ ሳይሆን የወሰን አንድነት የነበረው አንድነት ፓርቲ የሚናፍቀው ሥርአት፣ የመረረ የመብትና የነፃነት ጥያቄ ቀስቅሶ በየአቅጣጫው በተከፈተ የብሄራዊ ነፃነት የትጥቅ ትግል አገሪቱ ላይ የመበታተን አደጋ ደቅኖ የነበረ መሆኑን የአንድነት አመራሮች የማስታወስ ፍላጎት የላቸውም።

አንድነት በዚህ አኳኋን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ነባራዊ የፖለቲካ ሁኔታ ላይ የተንሸዋረረ ዕይታ ያለው ፓርቲ ሆኖ ሳለ የአውሮፓ ህብረት ሰለኢትዮጵያ ለማወቅ አንድነትን ማነጋገር ምን ሊፈይድለት ነው? የአውሮፓ ህብረት አጠቃላይ የኢትዮጵያ ፖለቲካ አሁን ያለበትን ሁኔታ ከአንድነት ፓርቲ ለመረዳት ያደረገው ሙከራ ዕውነተኛውን የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ገፅታ ሊያሳየው አይችልም። እዚህ ላይ ታዲያ የአውሮፓ ህብረት ዲፕሎማቶች የተባሉት ግለሰቦች የአንድነትን አመራሮች ማነጋገር ለምን ፈለጉ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው።

አንግዲህ ከቅርብና ከሩቅ ታሪክ እንደምናውቀው በተለይ አክራሪ ሊበራል የፖለቲካል ኢኮኖሚ መርህ ላይ የተመሰረቱ ምእራባውያን የአውሮፓ ሃገራት፣ በተለይ በማደግ ላይ ያሉ አገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ እነርሱ በሚከተሉት የፖለቲካል ኢኮኖሚ መርህ አቅጣጫ ብቻ መጓዝ አለባቸው የሚል አቋም ነው ያላቸው፡፡ እነዚህ የአውሮፓ አገራት ይህ እናውቅላችኋለን ባይነታቸው ከቅኝ ግዛት ፖሊሲዎቻቸው ጀርባ የነበረና አሁንም ውስጥውስጡን የሚከተሉተ የተዋሃዳቸው አመለካከት መሆኑንም እንረዳለን።

ምርጫ 97ን አስታኮ ስልጣን በኃይል ለመመንተፍ የተደረገው ሙከራ ላይ የአውሮፓ ሕብረት የፓርላማ አባልና የህብረቱ የምርጫ ታዛቢ ልኡክ መሪ የነበሩት ግራ አጋቢዋባለቴት፣ ወ/ሮ አና ጎሜዝ የነበራቸውም ሚና የቅርብ ግዜ ትውስታችን ነው፡፡ እነዚህ የአንድነት አመራሮችን አነጋገሩ የተባሉ የአውሮፓ ሕብረት ዲፕሎማቶች የአና ጎሜዝ የመንፈስ ልጆች የማይሆኑበት ምክንያትስ ምንድነው? እውነታው ወደዚህ የሚያደላ ነው።

አሁን በኢትዮጵያ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት የአገሪቱን ሕዝብ ደረጃ በደረጃ ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችል ነፃ የገበያ ኢኮኖሚን ከአገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር ባገናዘበ መልኩ መርህ ነድፎ (ልማታዊ ዴሞክራሲ የፖለቲካል ኢኮኖሚ መርህ)፣ በዚህ መርህ መሰረት ስትራቴጂና ፖሊሲ ቀረፆ፣ ዕቅድ ነድፎ ተግባራዊ እያደረገ ነው፡፡ በዚህ አካሄዱ የህዝቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ኑሮ ላይ ተጨባጭ መሻሻል ያመጡ የልማት ስኬቶችንም አስመዝግቧል፡፡ ይህን ስኬት የአውሮፓ ሕብረትና አባል አገራቱ፣ ሌሎች ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ተቋማትም ተቀብለውታል።

ይህ የኢትዮጵያ መንግስት የሚከተለው የፖለቲካል ኢኮኖሚ መርህ ሰሞኑን አንድነትን አነጋገሩ ከተባሉ የአውሮፓ ህብረት አባል ሃገራት መሃል አብዛኞቹ ከሚከተሉት አክራሪ የሊበራል ኢኮኖሚ መርህ የተለየ ባህሪያት አሉት፡፡ በዚህ አቅጣጫ ኢትዮጵያ እያስመዘገበችው ያለው እድገት ለሌሎችም በማደግ ላይ ያሉ አገራት ተምሳሌት መሆኑ አይቀሬ ብቻ ሳይሆን አሁንም መታየት ጀምሯል።

ይህ ሁኔታ አክራሪ የሊበራል ኢኮኖሚ አቀንቃኞች ለሆኑ አገራት የርዕዮተ አለም የበላይነትን የሚጋፋ ሆኖ ስለሚታያቸው፣ በተስፋፋበት ልክ ዓለምአቀፍ ተፅእኗቸውም የሚላላ ሆኖ ስለሚታያቸው አልተመቻቸውም፡፡ የኢትዮጵያን ህዝብ ከድህነት ለማወጣት የተሻለ መሆኑ ምንም ሳያሳስባቸው ለአክራሪ ኒዩሊበራሎች ስለማያስደስት ብቻ መገታት አለበት የሚል እምነት እንዳላቸው በተለያዩ አጋጣሚዎች በተግባረ አሳይተዋል፡፡ በሌሎች አገራትም ላይ በተለይ በምስራቅ አውሮፓ ሃገራት እስካሁን ድረስ የሚወስዱት እርምጃም ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡ ባለፉ አስር አመታት በተለይ በምስራቅ አውሮፓ አገራት የተካሄዱ እንዲሁም ምርጫ 97ን ተከትሎ በኢትዮጵያ የተሞከረው የቀለም አብዮት የተሰኘ ህገወጥ የመንግስት ለውጥ እንቅስቃሴዎች ለዚሕ አስረጂነት ሊጠቀሱ ይችላል።

ታዲያ አክራሪ ሊበራሎቹ የአውሮፓ ሃገራት፣ ባለፀጎቻቸውና በገንዘብ እየደገፉ የመሰረቷቸው ተቋሞቻቸው፣ ሕገወጥ የመንግስት ለውጥ ለማካሄድ፣ የታዳጊ አገራትን እጅ በመጠምዘዝ በሚፈልጉት አቅጣጫ ለመጎተት አጋዥ አገር በቀል አካል ያስፈልጋቸዋል፡፡ በምስራቅ አውሮፓ አገራት በኢትዮጵያም በተካሄዱትና በተሞከሩት የቀለም አቢዮት የመንግስት ለውጥ እንቅስቃሴዎችም ይህንኑ ስልት ነበር የተከተሉት።

ሰሞኑን የአውሮፓ ህብረት ልኡካን ተብዬዎቹን የተቀበለው አንድነት ደግሞ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በአዲሲቱ ኢትዮጵያ ውስጥ በህዝብ ውክልና ወደስልጣን መምጣት የሚያስችለው አቋም የሌለው በመሞት ላይ ያለ አመለካከት ላይ የተመሰረተ ፓርቲ ነው። ደጋፊዎቹ ለስልጣን ማብቃት የማይችሉ የአሮጌዎቹ ስርአቶች ውርዴ የሆኑ በተለይ አዲስ አበባ የሚኖሩና እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡

አንድነት ፓርቲ በብሄራዊ ማንነት ላይ የተመሰረተውን ፌደራላዊ ሥርአት አፈራርሶ ቀድሞ የነበረውን መዋቅር የመመለስ አቋም ያለው በመሆኑ የፌደራል መንግስቱን በመመስረቱና የፌደራል መንግስቱ የስልጣን ምንጭ በሆኑት ክልሎች፣ ማለትም፤ በኦሮሚያ፣ የኢትዮጵያ ሶማሌ፣ ቤንሻንጉል፣ ትግራይ፣ ጋምቤላ፣ አፋር፣ ሃራሬና ደቡብ ብሄሮችና ብሄረሰቦች ዘንድ በአብላጫው የአማራ ብሄር አባላትም ጭምር ምንም ድጋፍ ማግኘት እንደማይችሉ ግልፅ ነው፡፡

በመሆንም አንድነት በእነዚህ ክልላዊ መንግስታት ውስጥ፣ እንዲሁም ከየክልሉ በሚወከሉ እንደራሴዎች በሚዋቀረው የፌደራሉ መንግስት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ የመንግስት ሥልጣን ለመረከብ የሚያስችል የህዝብ ድምፅ የማግኘት እድሉ የሌለ ያህል የሚቆጠር ነው፡፡

አንድነት ሥልጣን ላይ ለመውጣት የተረፈው  አንድ አማራጭ ብቻ ነው፡፡ ይህም ማደናገሪያና መበጥበጫ መንገድ  አበጃጅቶ፣ ከሕዝብ ውክልና ውጭ ሥልጣን መመንተፍ ወይም መዝረፍ ብቻ ፡፡ ለዚህ ዓላማ መሳካት ከዚህ ቀደም በምስራቅ አውሮፓ አገራት የተካሄደው አይነት የቀለም አብዮት ማካሄድ ቀዳሚው ስልት ነው። ይህ ደግሞ የአክራሪ ሊበራል አቋም አራማጆችን ድጋፍ ይሻል፡፡ “የቀለም አቢዮት” የተባለው ምርጫን አስታኮ የሚቀሰቀስ ሕገወጥ የመንግስት ለውጥ ስልትን የፈጠሩትና እንዲካሄድ ያደረጉት እነዚህ አክራሪ ሊበራሎች መሆናቸው ሊታወስ ይገባል፡፡

እንግዲህ አክራሪ ሊበራል አውሮፓውያኖች ኢትጵያን በፈለጉበት አቅጣጫ እንደከብት ለመሳብ የሚያግዛቸው አካል ይፈልጋሉ፡፡ ለኢትዮጵያ ህዝብ መብት፣ ዘላቂ ጥቅምና ፍላጎት ደንታ የሌለው ባረጀና በመሞት ላይ ባለ አመለካከት ላይ የተንጠለጠለው አንድነት ደግሞ ስልጣን ለማግኘት ያስችለኛል ብሎ ካሰበ በማንም ቢሆን ለመነዳት ዝግጁ ነው፡፡ የአውሮፓ ሕብረት ዲፕሎማቶች በተባሉት የአና ጎሜዝ ውላጆችና በአንድነት መሃከል ያስተዋልነው የሰሞኑ ፍጥምጥም በዚህ ላይ የተመሰረተ ከመሆን የዘለለ አይደለም፡፡

የአንድነትና የአውሮፓ ሕብረት የተወሰኑ ዲፕሎማቶች ለየዓላማቸው ሥኬት ፍጥምጥም ፈፅመውብታል ተብሎ በሚገመትበት በዚህ አጋጣሚ የአንድነት አመራሮች የአና ጎሜዝ ወራሽ ለሆኑ የአውሮፓ ሕብረት ዲፕሎማቶች በኢትዮጵያ ላይ መወሰድ አለበት ያሉትን እርምጃ መጠቆማቸውንም ነግረውናል። ይህም “የሕብረቱ ድጋፍ በሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በማጠናከር በኩል መሆን ሲገባ ለአገዛዙ ጉልበት እየሰጠ ነው፡፡ ከዚህ ይታቀብ” የሚል ነው፡፡

እርግጥ ነው የአወሮፓ ሕብረትና ለጋሽ አገራት ለኢትዮጲያ ሰብአዊ እርዳታ በመስጠት ይታወቃሉ። ከዚም አልፈው ለዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚያግዝ የኢኮኖሚ ድጋፍ -

እርዳታና ብድር የሚሰጡበትም ሁኔታ አለ፡፡ ከዚህ ውጭ "የመንግስት ጉልበት ያፈረጥማል" ሊያስብል የሚችል ለጦር መሳሪያ ግዥ፣ ለወታደራዊ ስልጠናና መሰል ጉዳዮች የሚውል ድጋፍ አይሰጡም፡፡ ከዚህ በመነሳት የአንድነት አመራሮች "ለአገዛዙ ጉልበት የሚሰጡ" በሚል ያነሱት የአውሮፓ ሕብረት ድጋፍ የትኛው እንደሆነ በግልፅ ማወቅ ይቻላል፡፡ "የመንግስትን ጉልበት አፈርጣሚ" የተባለው የልማት እርዳታ ነው ፡፡ አንድነት እንዲቆም የጠየቀውም ይህንኑ እርዳታ ነው፡፡

አንድነት የልማት እርዳታ እንዲቆም ያለው ፍላጎት አዲስ አይደለም፡፡ ምርጫ 97ን ተከትሎ በውጭ በውጭ የሚኖሩ ፅንፈኛ የኢትዮጵያ መንግስት ተቃዋሚዎች የሞከሩት፣ አሁንም ባገኙት አጋጣሚ በሙሉ የሚጮሁበት ጉዳይ ነው፡፡ አንድነትና መሰሎቹ የልማት ድጋፍ ላይ ያላቸው የመረረ ተቃውሞ ተስፋው የተሟጠጠና መጪው ሕይወቱ የጨለመ ሕዝብ እንዲኖር ያላቸውን ፍላጎት ያሳያል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ካለፉት ስርአቶች የወረሰውና ለዘመናት ተጭኖት ከኖረው ድሕነት ውስጥ በአጭር ግዜ ለመውጣት ምርታማነቱን ለማሳደግ፣ መሰረተ ልማት ለማስፋፋት የሚውል ድጋፍ እንዳያገኝ የማድረግ ፍላጎት ነው፡፡

አንድነት በድህነት ውስጥ ያለ፣ ከድህነት መውጫ መንገድ የጠፋው፣ ተስፋው የጨለመ ሕዝብ እንዲኖር ለምን ፈለገ? መልሱ አጭርና ግልፅ ነው፡፡ ድሕነት የዋጠውና ተስፋ የቆረጠ ሕዝብ በቀላሉ የአመፅ መሳርያ ሊሆን በመቻሉ አንድነት ሕዝቡን ለዚህ ዓላማ የመጠቀም ጉጉት ያለው ከመሆኑ የመነጨ ነው፡፡

ይህ ዕውነታ፣ አንድነት " ከውስጡ ነው የወጣሁት፣ ተቆርቋሪው ነኝ፣ መብቱ ተጣሰ፣ ታፈነ . . ." እያለ የሚነዛነዘው ለሕዝቡ በማሰብ ሳይሆን የስልጣን ጥሙን ለማሳካት የሚያገለግል መሳሪያ አድርጎ ሊጠቀምበት መሆኑን በግልፅ ያሳያል፡፡ አንድነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለግዚያዊ ፍላጎቱ መጓደል፤ የምግብ ፣ የአልባሳት ፣ የመድሃኒት እጥረት . . .ከሚውል ሰብአዊ እርዳታ ያለፈ ድህነትን ለዘለቄታው እንዲያሸንፍ ማድረግ የሚያስችል የኢኮኖሚ ድጋፍ እንዳይሰጥ ያለው ፍላጎት ለቀለም አቢዮተ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ካለው ዓላማ የመነጨ ነው፤ ከዚህ የተለየ ምድራዊ ምክንያት የለውም፡፡